# የግል መረጃዎን ለእኛ (ለ Crisis) ማጋራት

- **እኛ የእርስዎን ዝርዝር የግል መረጃ ለምን እንጠይቃለን**
- **በመረጃዎቹ ምን እናደርጋለን**
- **መብቶችዎን መረዳት**

## ለምን መረጃዎን እንደምንጠይቅ እና እንደምናስቀምጥ

እኛን (Crisisን) ለእርዳታ ሲጠይቁ እና እንደ አባል ሲቀላቀሉን የተወሰኑ የግል መረጃዎችን እንጠይቅዎታለን። ይህ መረጃ ለእኛ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህም መኖሪያ ቤት በተሳካ ሁኔታ እንዲያገኙ የሚያስፈልግዎትን ድጋፍ ለእርስዎ ለመስጠት ከእርስዎ ጋር አብረን እንድንሠራ ይረዳናል።

እንዲሁም አገልግሎቶቻችን በጥሩ ሁኔታ እየሰሩ (ውጤታማ) መሆናቸውን ለማረጋገጥ የእርስዎን መረጃ እንጠቀማለን።

መረጃዎን የምንጠቀምበት ሌላው መንገድ ፖሊሲዎችን ለመለወጥ እና ለወደፊቱ የቤት እጦትን ለመቀነስ ስራችንንለ ማገዝ ነው። እኛ መረጃዎን በዚህ መንገድ በምንጠቀምበት ጊዜ እርስዎ እንደግለሰብ ማንነትዎ አይገለፅም ወይም አይታወቅም።

የተወሰኑ ነገሮችን ሲነግሩን ምቾት የማይሰማዎት ከሆነ መረጃ መስጠት የለብዎትም። ግን ሁሉንም አገልግሎቶቻችንን ለመጠቀም ከፈለጉ ለእኛ መስጠት ያለብዎት የተወሰነ መረጃ ይኖራል።

የCrisis አባል ሲሆኑ ከእኛ ጋር ወደ አንድ ጉዳይ ዝግጅት ይገባሉ። በእርስዎ የመኖሪያ ቤት ሁኔታ ላይ እርዳታ እና ድጋፍ እንሰጣለን። በምላሹም፣ እኛ ትክክለኛውን እርዳታ ለእርስዎ ለመስጠት የሚያስፈልገንን መረጃ እርስዎይሰጡናል። ይህ ዝግጅት እንደ 'ኮንትራት' ሊታይ ይችላል፣ እና እርስዎ መቀጠል የማይፈልጉበት ጊዜ ሲኖር ሊነግሩን ይችላሉ።

ስለእርስዎ እና ስለሌሎች አባላት መረጃ ለመሰብሰብ እና መረጃውን ለማስኬድ ህጋዊ መሰረት (ትክክለኛ ህጋዊ ምክንያት) ሊኖረን ይገባል። ሕጋዊነት ያለው መሰረት የሚያጠቃልለው፣ ፖሊሲዎችን ለመለወጥ እና አገልግሎቶቻችን የተሻለ እንዲሆኑ ዕገዛ ማድረግን ጨምሮ፣ እኛ እንደ አንድ ድርጅት ሥራችንን በአግባቡ እንድንሠራ መረጃ የመጠየቅ ፍላጎታችን ጭምር ነው። ይህ ህጋዊ መሰረት አግባብነት ያለው ፍላጎት ይባላል።

እንዲሁም የእኛ ኮንትራት ውል ዝግጅት የእርስዎን መረጃ እንድንሰበስብ እና መረጃውንእንድናስኬድ (እንድናከናውን) ሕጋዊነት ያለው መሠረት ይሰጣል።

በመጨረሻም፣ የሰዎችን ደህንነት ለመጠበቅ ያግዘን ዘንድ፣ የተወሰነ መረጃ መሰብሰብ ለእኛም አስፈላጊ ነው። ይህ ህጋዊ መሰረት የእርስዎን አስፈላጊ ፍላጎቶች መጠበቅ ይባላል።

## መረጃዎን እንዴት ደህንነቱ ተጠብቆእንደምናስቀምጠው

የሰጡንን መረጃ (የእርስዎን 'ዳታ') በኮምፒዩተር ስርዓታችን ላይ ደህንነቱን ጠብቀን እንዲቀመጥ እናደርጋለን። መረጃዎ በእኛ የCrisis ቡድን አባላት እርስዎ የሚሰሩትን ሥራ ለማገዝ ሲባል በጥንቃቄ ጥቅም ላይ ይውላል። ሰራተኞቻችን የሰለጠኑ ሲሆን የእርስዎን ግላዊነት የመጠበቅን አስፈላጊነት ይረዳሉ።

## መረጃዎን ለሌሎች ድርጅቶች ማጋራት

ሌሎች ድርጅቶች ፍላጎቶችዎን ለመደገፍ በተሻለ ሁኔታ ላይ ከሆኑ፣ እኛ ስለ እርስዎ የተወሰነ መረጃ ለነዚህ ድርጅቶች ልናጋራ እንችላለን፣ ነገር ግን እኛ ይህን የምናደርግ ከሆነ እርስዎ ስምምነትዎን (ፈቃደኝነትዎን) መስጠት በማይፈልጉባቸው ሁኔታዎች ሁልጊዜ እንነግሮታለን። የዚህ ምሳሌዎች ከሕዝብ ዘርፍ ድርጅቶች ወይም በሕዝብ የገንዘብ ድጋፍ ከሚደረግላቸው ድርጅቶች ጋር በምንሠራበት ጊዜ ሊሆን ይችላል። በእነዚህ አጋጣሚዎች፣ መረጃን ማጋራት ለሕዝብ ጥቅም ከሆነ መረጃውን ልንጋራ እንችላለን።

ያለፈቃድዎ መረጃን የምንጋራባቸው ሌሎች ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ለጉዳት ተጋላጭነት አለው ብለን የምናምንበትን ማንኛውንም ሰው (እርሶን ጨምሮ) ደህንነቱ እና ጤንነቱ ለመጠበቅ ፤ እና
- ፖሊስ ከባድ የወንጀል ምርመራን ለመደገፍ መረጃ ከጠየቀን ወይም በፍርድ ቤት ከተነገረን።.

## የእርስዎ ስምምነት አስፈላጊ ነው

እርስዎ ወደ እኛ ካልተላኩ (ካልተጠቆሙ) እና እርስዎን የላከልን ድርጅት ከእኛ ጋር በሆኑበት ቅጽበት እኛ በብቃት እንድንደግፍዎ ተጨማሪ ሚስጥራዊነት ያለው መረጃ ካላካፈሉን በስተቀር ስለ እርስዎ ያለን አንዳንድ መረጃ ወደ ዳታቤዝ ልንጨምር አንችልም።

ይህ መረጃ የሚከተሉትን ያካትታል፤

- የእርስዎ የዘር ወይም የብሔር ምንጭ፤
- የጤና መረጃ፤
- የእርስዎ ሃይማኖታዊ እና ፍልስፍናዊ እምነቶች፤
- የእርስዎ ወሲባዊ ዝንባሌ፤
- ባዮሜትሪክ መረጃ (ልዩ አካላዊ ባህሪያት፣ እንደ የእርስዎ የጣት አሻራዎች)፣ ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ ይህን አይነት መረጃ ባንሰበስብም፤ እና
- ባለፉት ጊዜዎች ተፈጽመው ሊሆኑ የሚችሉ የወንጀል ጥፋቶች ዝርዝሮች።

እኛ የእርስዎ ስምምነት እንዳለን ወይም ይህን አይነት መረጃ ወደ ዳታቤዝ ስንጨምር የእርስዎን መስማማት ማግኘታችንን ሁልጊዜ እናረጋግጣለን።

ሌሎች ማንኛቸውንም መረጃዎ ከሰበሰብንበት በተለየ ምክንያት የእርስዎን መረጃ መጠቀም ካስፈለገን፣ ለምን እና እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል እናሳውቅዎታለን። ለምሳሌ፣ መረጃዎን በምርምር ወይም በፖሊሲ ሥራችን ውስጥ ማንነትዎን ለመለየት በሚያስችል መንገድ ለመጠቀም ከፈለግን፣ ሁልጊዜም በመጀመሪያ የእርስዎን ፈቃድእንጠይቅዎታለን።

የSkylight ማዕከልን፣ ከቢሮዎቻችን አንዱን ወይም የCrisis ካፌን ሲጎበኙ በ CCTV ሊቀረፁ ይችላሉ። እኛ CCTVን የምንጠቀምበት ምክንያት ከእኛ ጋር የሚሰሩ ወይም የሚጎበኙን ሰዎች ጤንነታቸውን እና ደህንነታቸውን ለመጠበቅ፣ እና በግቢያችን ውስጥ የሚከናወነውን ማንኛውንም የወንጀል እንቅስቃሴ ለመከላከል እና ለማየት ነው። እኛ ይህንን የምናደርግ ከሆነ (በህንፃዎቻችን ውስጥ ባሉ ምልክቶች አማካኝነት) ሁልጊዜ እንነግርዎታለን።

## የእርስዎን መረጃ ስንሰበስብ

የሚሰጡን መረጃ እርስዎ ከእኛ ጋር በሚቆዩበት ጊዜ በኮምፒዩተር ዳታቤዝ ላይ ይሰበሰብ እና ይዘመናል።

ብዙውን ጊዜ መረጃን በሚከተሉት ደረጃዎች እንሰበስባለን።

- ለመጀመሪያ ጊዜ እኛን በሚቀላቀሉበት ጊዜ፣ ወደ እኛ ተልከውም (ተጠቁመውም) ቢሆን ወይም በቀጥታ ቢመጡም።
- ከእርስዎ ጋር መስራት በቀጠልንበት ጊዜ።
- ኮርሶችን ከእኛ ጋር ሲወስዱ ወይም አገልግሎቶቻችንን ሲጠቀሙ።
- እርስዎ የራስዎ የሆነ አስተማማኝ መኖሪያቤት ሲያገኙ።
- እርስዎ ከእንግዲህ የእኛን ድጋፍ እንደማይፈልጉ ሲወስኑ።
- ከአገልግሎቶቻችን ከወጡ በኋላ ተጨማሪ ድጋፍ እንደማያስፈልግዎት ለመፈተሽ ብሎም ስለእርስዎ ያሉንን መዝገቦች ማዘመን እንድንችል መረጃዎን ለማጋራት ከተስማሙ።

## መረጃዎን እንዴት እንደምንሰበስብ

አብዛኛውን የያዝነውን መረጃ ልትሰጡን ይችላሉ፣ ነገር ግን አንዳንድ መረጃዎች እርስዎን ወደ እኛ ለላኩልን ድርጅቶች ይጋራሉ። እርስዎ አብረዋቸው የሚሰሩት ሰራተኞቻችን፣ ለምሳሌ የእርስዎ መሪ ሰራተኛ፣ ከእኛ ጋር በሚኖሩበት ጊዜ ስላለ የእርስዎ መረጃም ወደ ዳታቤዛችን ሊጨምሩ ይችላሉ።

ከCrisis ውጭ የተሳተፉባቸው ድርጅቶች፣ እንደ ሌሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም የእንግዳ ማረፊያ አቅራቢዎች፣ የምክር ማዕከላት፣ የአከባቢ ባለሥልጣናት ወይም በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ያሉ ኤጀንሲዎች (ለምሳሌ የአመክሮ አገልግሎቶች)፣ ስለ እርስዎ ለእኛ መረጃ ሊሰጡም ይችላሉ። እነርሱ ለህዝብ ጥቅም ማጋራት ካለባቸው በተጨማሪ፣ ይህንን መረጃ የሚያጋሩት እርስዎን ወይም ሌላ ሰውን ሊደርስ ከሚችል ጉዳት ለመጠበቅ እርስዎ ከተስማሙ ወይም የማካፈል ህጋዊ ግዴታ ሲኖርባቸው ብቻ ነው።

## ስለእርስዎ የምንጠብቀው የመረጃ ዓይነት

የምናስቀምጠው መረጃ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል።

- የአድራሻዎ ዝርዝሮች (አድራሻ፣ ስልክ እና ኢሜል)
- ከእኛ ስለፈለጓቸው የእርዳታ አይነቶች መረጃ እና ምክንያቶቹ።
- ስለ አካላዊ እና አእምሯዊ ጤንነትዎ መረጃ። (የጤና እና ደህንነት እና የመጠበቅ/የከለላ ተግባሮቻችንን ለማሟላት ይህ መረጃ ሊያስፈልገን ይችላል።)
- ከእርስዎ ጋር ወይም ስለእርስዎ መገናኘት (ለምሳሌ፣ የእርዳታዎች መብትዎን የተመለከቱ ለእርስዎ የመጡ ደብዳቤዎች)
- እርስዎ ይገባኛል ብለው ለመጠየቅ የሚፈልጉትን ማንኛውንም ወጪ የሚደግፍ መረጃ
- እርስዎ የስቴት ጥቅሞችን የማግኘት ብቁነትዎ
- የቅርብ ዘመድዎ እና የአደጋ ጊዜ ተጠያቂ ዝርዝር መረጃዎ
- ለመኖሪያ ቤት እንዲያመለክቱ እየደገፍንዎት ከሆነ የቤተሰብዎ ዝርዝሮች።
- የዜግነት መረጃዎ
- የብቃት እና የሥልጠና መዝገቦችን ጨምሮ ስለ የቀድሞ ሥራዎ መረጃ
- ስለ ያልተቃለሉ/ያልተወራረዱ የወንጀል ፍርዶች (ማሳወቅ ያለብዎት) ወይም የወንጀል ሰለባ ስለነበሩበት ቦታ መረጃ።
- እርስዎን በሚደግፉ ሰራተኞቻችን የተዘጋጁ ሰነዶች እና ኢሜሎች

## መረጃዎን ለምን ያህል ጊዜ እንይዘዋለን

ምክር ወይም መመሪያ በኢሜል ፣ በስልክም ሆነ በአካል ከጠየቁን እና አገልግሎቶቻችንን ለረጅም ጊዜ ለመጠቀም ካልቀጠሉ ፣ እርስዎን ከረዳን በኋላ መረጃዎን ለስድስት ወራት ያህል እናቆየዋለን ።

ሆኖም ግን፣ አብዛኛዎቹ ሰዎች ከኛ ጋር ረዘም ላለ ጊዜ ይሰራሉ። ሁኔታው ይህ ከሆነ፣ አገልግሎቶቻችንን መጠቀም ካቆሙ በኋላ አብዛኛዎቹን የግል መረጃዎችዎን ለሰባት  ዓመት ያህል እንይዛቸዋለን። አንዳንድ ጊዜም ረዘም ላለ ጊዜ ማቆየት ሊኖርብን ይችላል። ይህ ያልተለመደ ነገር ነው፣ ነገር ግን አንዳንድ ድርጅቶች እርስዎ የሚጠቀሙባቸውን አገልግሎቶች በገንዘብ የሚደግፉ ከሆነ፣ የመረጃ ዝርዝሮችን ረዘም ላለ ጊዜ እንድናቆይ ሊጠይቁን ይችላሉ።

ከሰባት ዓመታት በኋላ፣ እርስዎን የሚለይዎትን/የሚያሳውቅዎትን ማንኛውንም ነገር ከግል መረጃዎ እናስወግዳለን እና የቤት እጦት መንስኤዎችን እና ሰዎችን እንዴት ከዚህ ችግር ለማውጣት እንደምንረዳ ለማወቅ የምናደርገውን ጥናትና ምርምር ለመቀጠል ይረዳን ዘንድ ይህን ማንነትን የማያሳውቅ መረጃ እንይዘዋለን።

## መብቶችዎ እና መረጃዎ

መረጃዎ ጥቅም ላይ እንዴት እንደሚውል በተመለከተ መብቶች እና የመቆጣጠር ችሎታ አሉዎት። ይህንን እንዲያደርጉ የሚረዱዎት ህጎች የUK አጠቃላይ የመረጃ ጥበቃ ደንብ (GDPR) እና የዳታ (መረጃ) ጥበቃ ሕግ 2018 (DPA) ናቸው።

በእነዚህ ህጎች መሰረት፣ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ።

- እኛ ስለእርስዎ ያለንን መረጃ በሙሉ እንድናሳይዎት እርስዎ ሊጠይቁን ይችላሉ። (ይህን ሂደት ከእኛ የዳታ (መረጃ) ጥበቃ ቡድን ጋር እንዲጀምር መሪ ሰራተኛዎን መጠየቅ ይችላሉ።)
- በስርዓታችን (በሲስተማችን) ውስጥ ስለእርስዎ ስህተት ነው ብለው የሚያስቡትን ማንኛውንም ነገር እንድናስተካክል መጠየቅ ይችላሉ።
- የእርስዎን ግላዊ መረጃ ከስርዓታችን እንድንሰርዝ መጠየቅ ይችላሉ። (ይህንን ማድረግ የማንችልባቸው ጊዜያት ሊኖሩ ይችላሉ – ለምሳሌ፣ የጉዞ ወጪዎቻችሁን ተክተንላችሁ ከሆነ፣ በህግ አግባብ ለእርስዎ የከፈልንባቸውን ክፍያዎች ዝርዝር መያዝ አለብን።)
- በመረጃዎ የአሰባሰብ እና መረጃዎን  የማስኬድ ምክንያቶቻችን ደስተኛ እንዳልሆኑ ሊነግሩን ይችላሉ።
- መረጃዎን ለሌላ ተመሳሳይ አገልግሎት አቅራቢ (በተቻለ መጠን እና በተወሰኑ ሁኔታዎች) እንድናስተላልፍ ሊጠይቁን ይችላሉ።
- ሃሳብዎን ሊቀይሩ ይችላሉ። (መረጃዎን እንድናስኬድ እና እንድናቆይ ፍቃድ ከሰጡን በአንዳንድ ሁኔታዎች ይህንን ፈቃድ ማንሳት ይችላሉ።)
- የ GDPR ወይም የ DPA 2018 ሕጎችን ጥሰናል ብለው ካመኑ ቅሬታዎችን ማቅረብ ይችላሉ ።

### ቅሬታዎችን እንዴት ማቅረብ እንደሚቻል

በመረጃ ጥበቃ ላይ ቅሬታ ካለዎት የመረጃ ኮሚሽነር ቢሮን በ ico.org.uk/concerns/handling/ማግኘት ይችላሉ።

ነገር ግን፣ እኛ እርስዎን መጀመሪያ ለመርዳት ለመሞከር ሁልጊዜ እንፈልጋለን። ስለዚህ የእኛን የእርስዎን መረጃ አያያዝ በተመለከተ በሚያስቡት  ላይ ደስተኛ ካልሆኑ፣ እባክዎ በመጀመሪያ በSkylightማእከልዎ ዳይሬክተሩን ያነጋግሩ።

የመረጃ ጥበቃ ኦፊሰራችንን ኢሜል በ data.protection@crisis.org.uk በመላክ ማግኘት ይቻላል

እኛ (Crisis)ለዳታ (መረጃ) ጥበቃ ህግ 2018 እና UK GDPR ዓላማዎች የዳታ (መረጃ) ተቆጣጣሪ ነን።